- **ይሁዳ የመረጠው ‹ጌታ›**

ይሁዳ ጌታውን አሳልፎ ሊሠጥ ከመሔዱ ከሰዓት በፊት ጌታችን በቢታንያ በለምጻሙ ስምዖን ቤት ተገኝቶ ነበር:: ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ እንዳለው ዘማ የነበረችው ባለ ሽቱዋ ማርያም ይህንን ስትሰማ «በለምጻሙ ስምዖን ቤት ሳይጠየፍ ከተገኘና ከፈወሰው የእርስዋንም የነፍስዋን ዕድፍ እንደሚያነጻላት» ተስፋ አድርጋ ገሰገሰች:: በፍጹም ንስሓና የልብ መሰበር ወደ ጌታችን ቀርባ በውድ ዋጋ የገዛችውን የአልባስጥሮስ ብልቃጥ ሽቱ ያለ አንዳች ስስት በክርስቶስ ላይ አፈሰሰችው:: ቤቱ በናርዶስ ሽቱ መዓዛ ተሞላ:: የሴቲቱንም ንስሓም ጌታችን እንደ ሽቱው በጎ መዓዛ ተቀበለላት:: ይህ የሽቱ መዓዛ ግን ለአስቆሮቱ ይሁዳ አፍንጫ አስደሳች መዓዛ አልሆነም::

ቅዱስ አውግስጢኖስ «ለእነዚህ ለሞት የሚሆን የሞት ሽታ ፣ ለእነዚያም ለሕይወት የሚሆን የሕይወት ሽታ ነን» የሚለውን የቅዱስ ጳውሎስ ቃል በማጣቀስ «ሴቲቱ ካፈሰሰችው ሽቱ የሚወጣው የሕይወት ሽታ ለአስቆሮቱ ይሁዳ የሞት ሽታ ሆነበት» ይላል:: (፪ቆሮ. ፪፥፲፮) በእርግጥም የሽቱው መዓዛ የአንዲትን ነፍስ ወደ እግዚአብሔር መመለስ የሚያውጅ መዓዛ ነበር:: የሰማይ መላእክት በአንዲቱ የባከነች ኃጥእት ነፍስ መመለስ ደስ ሲሰኙ

Scanned with CamScanner

ይሁዳ ግን ያሳሰበው የሽቱው መባከን ነበር:: ከዚህች ሴት ነፍስ የ
ይልቅ የይሁዳ ጭንቅላት ሲያሰላ የነበረው «ሽቱው አሁን ባለው ገበያ ስን
ሊያወጣ ይችላል?» እያለ ነበር:: የአንዲት ነፍስ ዋጋዋ ከዓለም ሁሉ የ
ይበልጣል:: (ሉቃ. ፱፥፳፭) ይሁዳ ግን ከዓለም ከሚበልጠው የሰው ነፍስ
መመለስ ይልቅ የአንድ ብልቃጥ ሽቱ ጉዳይ አንገበገበው:: «ይህ ጥፋት
ምንድር ነው? ሽቱው ለሦስት መቶ ዲናር ተሸጦ ለድሆች ያልተሰጠ ስለ ምን ነው?
አለ» በተሰበረ ልብ ለመመለስ በጌታዋ ፊት ራስዋን ያዋረደችውን ሴት
የሚያሸማቅቅ ፣ የጥፋተኝነት ስሜት እንዲሰማት የሚያደርግና ጌታችን
እንዳለው ‹የሚያደክም› ንግግር ተናገረ::

ስለ ድሆች ማሰብ መልካም ነው:: ጌታችንም ‹ከሚቀበል ይልቅ
የሚሠጥ ብፁዕ ነው› ብሎ አስተምሯል ፣ ለድሆች ምጽዋት እንዲሠጥ
ግዘዙም ሐዋርያቱ ሲያዩት የኖሩት ልማድ ነበር:: (ሐዋ. ፳፥፴፫፣ ዮሐ.
፲፫፥፳፱) ሰዎችን መርዳት ግን ነፍሳቸውን ከማዳን ሥራ አይበልጥም::
በቤተ ክርስቲያን የሚደረግ ማንኛውም የርዳታ ሥራ ሁሉ ነፍሳትን ወደ
እግዚአብሔር አስተምሮ ከመመለስ አገልግሎት የበለጠ ሥፍራ
እንዲሰጠው ግድረግ የይሁዳን አስተሳሰብ ማራመድ ይሆናል:: እንደ
እውነታው ከሆነ ግን ይሁዳን ያስጨነቀው የድሆች ጉዳይ አልነበረም::
ቅዱስ ዮሐንስ «ይህንም የተናገረ ሌባ ስለ ነበረ ነው እንጂ ለድሆች ተገድዶላቸው

Scanned with CamScanner

አይደለም ፤ ከረጢትም ይዞ በውስጡ ከሚገባው ይወስድ ስለ ነበረ ነው» በማለት እውነታውን ጽፎልናል፡፡ (ዮሐ. ፲፪፥፮)

ይሁዳ ከሐዋርያት መካከል የሙዳየ ምጽዋቱ ባለ አደራ ነበር፡፡ «ከክፉዎች መናፍስትና ከደዌም ተፈውሰው የነበሩ አንዳንድ ሴቶች ፤ እነርሱም ሰባት ኢጋንንት የወጡላት መግደላዊት የምትባል ማርያም የሄሮድስ አዛዥ የኩዛ ሚስት ዮሐናም ሶስናም ብዙዎች ሌሎችም ሆነው በገንዘባቸው [ኢየሱስ ክርስቶስን] ያገለግሉት ነበር» (ሉቃ. ፰፥፫) እነዚህ ምእመናት ከደዌና ከመናፍስት እስራት ላላቀቃቸውና ስእለታቸውን (ልመናቸውን) ለሰማቸው ጌታ በፍቅር የሚሰጡትን ገንዘብ በከረጢት የሚይዘው የአስቆሮቱ ይሁዳ ነበር፡፡ ይሁዳ ምእመናን ከዕንባቸው ቀላቅለው ከሚሰጡት ፤ በፍቅር ከሚያበረክቱት ገንዘብ ላይ እያነሣ ለራሱ ይወስድ ነበር፡፡ ሦስት መቶ ዲናር ያወጣል ብሎ የገመተው ሽቱም ተሸጦ ቢሆን ኖሮ ቀድሞ የሚገባው ከድሆች ሳይሆን ከይሁዳ ኪስ ነበር፡፡

Scanned with CamScanner